‹‹ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከሥሩም
ቍጥቋጥ ያፈራል፡፡››

ኢሳ.፲፩፥፩

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

🖂 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



መልአከ ሕይወት ቀሲስ ንጉሤ አወቀ የሀድያ (ስልጤ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ)



ዶክተር ኢንጅነር ቶፊቅ ጀማል (የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት)

# የወራቤ ዩኒቨርስቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ችግር ላይ መሆናቸው ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ

በስልጤ ዞን ውራቤ ከተማና አካባቢው አክራሪ እስላሞች በፈጸሙት ሃይማኖት ተኮር ጥቃት የወራቤ ዩኒቨርስቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ለከፋ የፀጥታ ችግር ማጋለጣቸውን

የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሕይወት ቀሲስ ንጉሤ አወቀ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው የስልክ ቆይታ ገለጡ፡፡

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጣ በወራቤ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ይከታተሉ የነበሩ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች አክራሪ እስላሞች ባደረሱባቸው ሃይማኖት ተኮር ጥቃት በርካቶች የአካልና የሥነ ልቡና ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በሀገረ ስብከቱ መረጃ መሠረት ሠላሳ አንድ የሚሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን ከእነዚህ መካከል የአንድ ተማሪ ሕይወት አልፏል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም በሀገረ ስብከቱ ብርቱ ጥረት ጉዳት ከደረሰባቸው ተማሪዎች መካከል የተወሰኑት ከዩኒቨርስቲው ውጭ በሚገኙ የመንግሥት የጤና ተቋማት የሕክምና ክትትል እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልጠው ሌሎች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው አሥራ ሦስት ተማሪዎች ግን ከዩኒቨርስቲው ውጭ የተሻለ ሕክምና እንዳያገኙ የዩኒቨርስቲው አመራሮች

መከልከላቸውን ተናግረዋል፡፡

በወራቤ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ በነበሩ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ አክራሪዎች የአካል፣የሞትና የሥነ ልቡና ጉዳት ባደረሱበት ወቅት ተማሪዎች ከጉዳታቸው ሳያገግሙ ዩኒቨርስቲው ሚያዚያ ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ፈተና ለመፈተን መዘጋጀቱ ፀረ ኦርቶዶክስ ተግባር መሆኑን ያወገዙት ሥራ አስኪያጁ የመርሐ ግብር ማስተካከያ እንዲያደርግም ጠይቀዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አክለውም በኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ አክራሪዎች ካደረሱት ሁለንተናዊ ጥቃት በተጨማሪ አብያተ ክርስቲያን እንዳይቃጠሉና እንዳይዘረፉ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ ተማሪዎች በሙሉ መታሰራቸውን ጠቁመው የታሰሩ ተማሪዎችም በአስቸኳይ እንዲፈቱ አሳስበዋል፡፡

በወራቤ ዩኒቨርስቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ

እየተፈጸመ ያለው ወንጀል እጅግ አሳሳቢ መሆኑና ዩኒቨርስቲው በተማሪዎች ላይ ከጊዜ ወደጊዜ እያሳደረ ያለው ጫና የከፋ በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት፣ ለስልጤ ዞን አስተዳደር፣ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሀገረ ስብከቱ ደብዳቤ መጻፉን ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡

ሀገረ ስብከቱ በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ የተፈጸመውን ግፍ በትኩረት እየተከታተለው መሆኑን ያስረዱት ዋና ሥራ አስኪያጁ በችግሩ ዙሪያ መፍትሔ ለማምጣት አጠቃላይ በሀገረ ስብከቱ መዋቅር ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል፡፡ ከውይይቱ በኋላም የወራቤ ዩኒቨርስቲና የአካባቢው ማኅበረሰብ በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ እያደረሱ ያለውን መከራ ለቅዱስ ሲኖዶስ በደብዳቤ ማሳወቃቸውን አክለው አስረድረተዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም አክራሪዎች ያደረሱትን ጥፋት ለማጥናትና የተጎዱ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የተሻለ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ክልሉ በቂ የፀጥታ ኃይል እንዲመድብላቸው መጠየቃቸውን ተናግረው በቂ የፀጥታ ኃይል የሚመደብላቸው ከሆነ አጠቃላይ በስልጤ ዞን በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን ሀገረ ስብከቱ አጣርቶ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የወራቤ ዩኒቨርስቲ ዋና ፕሬዚዳንት ዶክተር ኢንጂኔር ቶፊቅ ጀማል ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በስልክ በነበራቸው ቆይታ ከወራቤ ዩኒቨርስቲ ውጪ ያለው የኅብረሰብ ክፍል ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ ገብቶ በተማሪዎች ላይ ሃይማኖት ተኮር ጥቃት እንዳይፈጽም ዩኒቨርስቲው የቻለውን ሁሉ ማድረጉን ተናግረዋል፡፡ “በዩኒቨረስቲው ያለውን የፀጥታ ስጋት ለመቅረፍ ከግቢው መደበኛ የጥበቃ አባላት በተጨማሪ በቂ የሆነ የክልሉን ልዩ ኃይል አሰማርተናል” ሲሉም አክለዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም “ዩኒቨርስቲው ለሚያዚያ ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ያወጣው የፈተና መርሐ ግብር በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች የሚመለከት አይደለም” ካሉ በኋላ “ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች ከጉዳታቸው ካገገሙ በኋላ ለብቻቸው የማካካሻ ትምህርት ተሰጥቷቸው ለፈተና የሚቀርቡ ይሆናል” ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ሁሉም ጉዳት የደረሰባቸው ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ተገቢውን እንክብካቤ እየተደረገላቸውና በቂ የሕክምና አገልግሎት እያገኙ መሆኑን አክለው ተናግረዋል፡፡

አክለውም “በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ወደፊት ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ቀድሞ ለመከላከል ግብረ ኃይል አቋቁመን እየሠራን ነው” ያሉት ፕሬዚዳንቱ “በአሁኑ ወቅት በየኒቨርስቲው ግቢ ምንም ዓይነት የፀጥታ ስጋት የለም” ብለዋል፡፡ ይህንንም ማንኛውም አካል በተግባር ማረጋገጥ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ የስልጤ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሙርሰል በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡን በእጅ ስልካቸው የደወልንላቸው ቢሆንም ምላሽ ሊሰጡን አልቻሉም፡፡

# ሀገረ ስብከቱ በስልጤ ዞን በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የደረሰውን ጉዳት እንዳያጣራ መከልከሉን አስታወቀ

*ካሳሁን ለምለሙ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት በስልጤ ዞን አክራሪዎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመና ላይ ያደረሱትን ጉዳት እንዳያጣራ መከልከሉን ሚያዚያ ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባወጣው መግለጫ አስታወቀ፡፡

ከዚህ ቀደም የዞኑ አክራሪ እስላሞች በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን፣ በቤተ ክርስቲያንና በሀብት ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድርሳቸውን ያሳወቀው ሀገረ ስብከቱ አሁንም ኦርቶዶክሰውያን እንግልት፣እሥር፣ድብደባና ወከባ እየተፈጸባቸው መሆኑን ገልጧል፡፡

የስልጤ ዞን የመንግሥት አመራሮች የተፈጸሙና እየተፈጸሙ ያሉ ሃይማኖት ተኮር ወንጀሎችን በማድበስበስና ወንጀሎኞችንም በመደበቅ መጠመዳቸውን የጠቆመው ሀገረ ስብከቱ በአንጻሩ ምንም ዓይነት የወንጀል ተሳትፎ የሌላቸው ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎችን ማሠርና ማዋከብ መቀጠላቸውን አስረድቷል፡፡ በአክራሪዎች ጉዳት የደረሰባቸው የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች በቂ ሕክምና ሳያገኙና ከነሕመማቸው ያለምንም ፍርድ ማረሚያ ቤት እተወሰዱ መሆኑን ያስታወቀው ሀገረ ስብከቱ በዞኑ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለማጣራት ለዞኑ ጥያቄ ቢቀርብለትም አወንታዊ ምላሽ እንዳላገኘ አስረድቷል፡፡

የዞኑ የመንግሥት አመራሮች ጥፋተኞችን ትተው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችንና ሌሎች ምእመናንን ያለበደላቸው ለመወንጀል ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ያሳወቀው ሀገረ ስብከቱ በተለይ በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ላይ አሁንም ድረስ ከፍተኛ በደል እየተፈጸመ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ለትምህርት ሚኒስቴር ደብዳቤ እንዲጽፍ አሳስቧል፡፡

በመጨረሻም አክራሪዎች በምእመናን፣በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በሀብት ንብረት ላይ ባደረሱት ጉዳት መንግሥት ኃለፊነቱን እንዲወስድ ያሳሰበው ሀገረ ስብከቱ ጉዳት ያደረሱ አካላትና የስልጤ ዞን አመራሮች በሕግ እንዲጠየቁ እንዲሁም ለደረሰው ጉዳት መንግሥት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ጠይቋል፡፡ በተያያዘ ዜና የስልጤና ሀድያ ሀገረ ስብከት በስልጤ ዞን በቤተ ክርስቲያን፣በምእመናንና በሀብት በንብረታቸው ላይ አክራሪዎች ያደረሱትን ጉዳት በሰለማዊ ሰልፍ ለማውገዝ ሚያዚያ ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደርን መጠየቁን አስታውቋል፡፡

# የጥፋት ኃይሎች ከቤተ ክርስቲያን ላይ እጃቸውን ያንሡ!

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ የሚደርስባትን ዘርፈ ብዙ መከራ ተቋቁማ ወንጌልን እየሰበከች በእሳት ውስጥ አልፋ እዚህ ብትደርስም፤ መኖሯ የሚያማቸው፣ ግርማ ሞገሷ የሚያስደነግጣቸውና የሚያስፈራቸው የዘመናት ጠላቶቿ ዛሬም አለመተኛታቸው የዐደባባይ ምስጢር ነው። ከፊት ቀድመው አገልግሎቷን ለማደናቀፍ፣ በውስጧ ሰርገው ገብተው አንድነቷን ለመበረዝ ብሎም እንድትጠፋ ለማድረግ ብዙዎቹ የየድርሻቸውን ሲሠሩ ኖረዋል›› ዛሬም ከዚህ ድርጊታቸው አልተቆጠቡም።

የግል ወይም የወል አጀንዳቸውን ለመፈጸም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከለላ ያደረጉ እኩያት በመጡና በሄዱ ቁጥር የመከራ ዶፍ ሲያዘንቡባት ኖረዋል። ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።›› (ዮሐ.፲፮፥፴፫) ተብሎ የተጻፈውን የወንጌል ቃል ተሸክማ አምላኳን በመምሰል ዘመን ይዞባት የመጣውን መከራ ሁሉ ተቋቁማ ብታልፍም ለሥውር ዓላማቸው ማስፈጸሚያ በማድረግ ከዋናው አገልግሎቷ እንድትወጣ ሲጥሩ የነበሩ በርካታ ናቸው። ይዘውት የመጡትን ፍልስፍና ተቀብላ እንድታራምድ እጆቻቸውን ወደ ጓዳዋ በመዘርጋት ለጥፋት ያዘጋጇትም ጥቂት አልነበሩም። ለዚህ ደግሞ በየዘመናቱ የተነሡ የሀገር መሪዎችና ፖለቲከኞች ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫውተዋል።

ቅጥሯን ለማፍረስ፣ መቅደሷን ለማርከስ፣ እምነቷን ለመበረዝ የደፈሩቱ፤ የእርሷ የሆነው ሁሉ የሚያምራቸው ኤልዛቤላውያን የእልፍ አእላፍ ልጆቿን ደም በከንቱ አፍስሰዋል። የሀገርን ታሪክ፣ እምነትና፣ ባህልን ጠብቀው የኖሩ ብርቅዬ አብያተ ክርስቲያናቷን፣ ገዳማቷን በአጠቃላይ ቅዱሳት መካናቷን ሲዘርፉ፣ ሲያቃጥሉ ኖረዋል። ዳሩ መሠረቷ የጌታ ደም ነውና ‹‹የገሃነም ደጆች አይችሏትም›› የተባለላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚያ ሁሉ መከራ ውስጥ አልፋ ዛሬም እንዳለች አለች። ሥጋ እንዳየ አሞራ ዙሪያዋን የከበቧት ጠላቶቿ በጥፋት ጥርሳቸው ሊቃረጧት አሰፍስፈው እንደሚጠብቋት የሚታወቀው በየጊዜው ቀናትንና ሰዓታትን ወራትን እና ዓመታትን እየጠበቁ የጥፋት ክንዳቸውን ሲያሳርፉባት ነው።

ኦርቶዶክስ ሀገርዋ የት ነው? ብለን እስክንጠይቅ ድረስ ሀገር አልባ፣ ይዞታ አልባ ፣ ክብር አልባ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ሲታይ ይህችን ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ለምን ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን። ምክንያት እየተፈለገ ለሚሸረሸረው ልዕልናዋ ተጠያቂዎቹ፣ አጥፊዎቹ ብዙ ናቸው። አንዱ የብሔር ካባ አልብሶ ወደ ፖለቲካው ሲያስጠጋት ሌላው ቅዱሳት መካናቷ ላይ ዓይኑን ጥሎ ሊነጥቃት ይተጋል።

ሌላው በማሸማቀቅ ውስጥ እንድትኖር ብሎም እንድትጠፋ አገልጋዮች ካህናቷንና፣ ጌጦቿና መድመቂያዎቿ የሆኑ ምእመናንዋን ይገድላል። ለዚህ ሁሉ ወደር የለሽ ግፍ አጥፊዎች ብዙዎች ሲሆኑ በዓላማ ግን አንድ ናቸው። እንደእነዚህ ያሉ ግፎችን መስማት እና ማውራት በራሱ ምንም አይፈይድም። ይህን ሁሉ ግፍና መከራ እየተቀበለች ያለችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሰቆቃ እየሰሙ ከንፈር መምጠጥና ዝም ብሎ ማንባት ሊበቃ ይገባል።

ትላንት ያለፈችበትን የሰቆቃ ኑሮ ዛሬም በከፋ መልኩ እየኖረችው፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደረጉ ነገሮች ከድጡ ወደ ማጡ እየሄዱ ነውና ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል። በሄተ ቤተ ክርስቲያን አንድ እንዳትሆን ከአባቶች ጀምሮ እስከ ምእመናን ድረስ እየተሠራ ያለው የመከፋፈልና በጥላቻ እንዲተያዩ የማድረጉ እኩይ ተግባር በቤተ ክርስቲያን ልጆች ግንዛቤ ሊወሰድበት፤ ጥንቃቄም ሊደረግበት ያስፈልጋል ጠላት የከፈታቸውን የመለያየት ቀዳዳዎች ኦርቶዶክሳውያን በብልሃት ሊደፍኑት፣አንድነትን በማጠንከር ስለ አንዲቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ልጆቿ እኩል ሊጮኹ ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን የነካችው ሁሉ የሚያምራቸው የጥፋት ኃይሎች የሚያደርጉትን ትንኮሳ ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ

በእኩል መቃወም አለበት። ክርስቲያኖችን በመግደል፣ በማሳደድ፣ በእምነታቸው እንዳይኖሩ ልዩ ልዩ ሥቃይ እንዲደርስባቸው ማድረግ ኦርቶዶክስ የማዳከም ትልቁ ዘመቻ ነው። በዚህ ወቅት እንደ ፋሽን የተያዘው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማቃጠል እና ንዋያተ ቅድሳቷን መዝረፍ ታሪክ አልባ ለማድረግ የሚደረገው ጉዞ ነው።

በዚህ ሁሉ የጥፋት ተልእኮ ውስጥ ለምእመናን እንባ ምላሽ አለመስጠት፣ ቤተ ክርስቲያንን አስቀድሞ አለመታደግ እንዲሁም አባቶች ለሚያነሡት ጥያቄ ጆሮ መንፈግ የነገዋን ቤተ ክርስቲያንን ተስፋ ለማጨለም የሚደረጉ ሩጫዎች ናቸውና ዛሬ ላይ ሥራ መሥራት ለነገ የማይባል ነው። መንግሥትም እንዲህ ዓይነቶቹን እኩይ ድርጊቶች በቸልታ ሳይመለከት ችግሮቹ ለሀገራዊ ቀውስ መንሥኤ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመረዳት ቤተ ክርስቲያንን የመታደግ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል እንላለን።

በየጊዜው ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሱ ያሉት ጫናዎች፤ ነገሮች ወደ አላስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ የሚደረጉ ገፋፊ ምክንያቶችን የቤተ ክርስቲያን ልጆች በውል በመገንዘብ ሁኔታዎችን በትዕግሥትና በጥበብ መያዝ ተገቢ ነው። የኛ የሆኑትን መጠበቅ፤ ለይቶ ማወቅ፤ ሲነኩ ለምን ብሎ መጠየቅ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሚጠበቅ ነው። ትላንት የነበሩ ፈተናዎች መልካቸውን ቀይረው ሲመጡ በዚያ ልክ ራስን ማዘጋጀት ከሁላችን ይጠበቃል።

ዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት የሚቃጠሉበት፣ ምእመናን የሚታረዱበትና የሚሰደዱበት እንዲሁም በአጠቃላይ ዕለት ዕለት የቤተ ክርስቲያንን ሰቆቃ የምንሰማበት ዘመን በመሆኑ ሁላችንም ዕለት ዕለት ስለቤተ ክርስቲያን ክብር መቆም፣ መቆርቆር ይጠበቅብናል። በክርስቶስ ደም ላይ የተመሠረተች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ያልተረዱ፤ በየዘመናቱ የተነሡ ታላላቅ ጠላቶቿን አሸንፋ እዚህ መድረሷን፤ አጥፊዎቿ ጠፍተው ዛሬም ድረስ የመዝለቋን ታሪክና ምሥጢር የማያውቁ የዘመናችን እኩይ የጥፋት ኃይሎች ቤተ ክርስቲያንን ገፍተው መጣል አይቻላቸውምና ከዚህ ጥፋታቸው ሊታቀቡ ይገባል እንላለን።

# ሞዐ ተዋሕዶ የቤተ ክርስቲያንን ጥያቄዎች ለማስመለስ እየሠራሁ ነው አለ

ክፍል ሁለት

*በሻምበል ጥላሁን*

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

መምህር ፋንታሁን ዋቄ ስለ ሞዐ ተዋሕዶ በንቅናቄው ማኅበራዊ ገጽ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ እንዳመለከቱት፤ ሞዐ ተዋሕዶ ፓርቲ አይደለም፣መምሪያ አይደለም፣ሰንበት ትምህርት ቤት አይደለም የኦርቶዶክሳውያንን ጩህትና ብሶት መልስ ለማሰጠትና ለማስተባበር በበጎ ፈቃደኝነት በምእመናን የተወከለና የተዋቀረ ግብረ ኃይል ነው ሲሉም ይብራራሉ፡፡

ሞዐ ተዋሕዶ የተባለው የንቅናቄ ግብረ ኃይል ስሙን ከግብሩ ጋር ለማዋሕድ ተብሎ ነው የሚሉት የግብረ ኃይሉ ሌላው አባል ዶክተር ወንድወሰን አሰፋ ናቸው፡፡ ዶክተር ወንደሰን እንደሚያስረዱት፤ ግብረ ኃይሉ ማኅበር ሳይሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ምእመናን ከግለሰብ እስከማኅበራት የድርሻቸውን የሚወጡበትና የሚሳተፉበት ጥያቄዎቻችንን በጋራ አቀናጅተን የምንጠይቅበትን መንገድ ለማመቻቸት ሁሉንም ባለድርሻ አቀናጅቶ ለማንቀሳቀስና በአንድ አጀንዳ ለመምራት የተቋቋመ የሁሉ ቤት እንጂ የሆነ ኃይል ለብቻው ሥራ የሚሠራበት ስብስብ አይደለም በማለት ግብረ ኃይሉን ይገልጻሉ፡፡

የሞዐ ተዋሕዶ መቋቋም ውጤት ያመጣል የሚል ተስፋ እንዳላት የምትናገረው ወ/ት ትእግስት ሙልነህ ፤ የግብረ ኃይሉ የአደረጃጀት ስብጥር፣ ቤተ ክርስቲያን እንዲፈታላት የምታነሳቸውን ጥያቄዎችን አጠቃሉና አደራጅቶ በሰባት ክፍሎ ያስቀመጠበት መንገድና በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ምእመናንን ለማስተባበር እየሄዱበት ያለው አካሄድ ግብረ ኃይሉ ውጤት ያመጣል የሚል ተስፋ እንድሰንቅ አድርጎኛል ትላለች፡፡

በቤተ ክርስቲያን ስም የሚመሠረቱ ብዙ ማኅበራት ከዚህ በፊት ብቅ ብቅ ብለው በዚያው መጥፋታቸውን የሚያነሳው ወጣት ጴጥሮስም ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› መብት ለማስጠበቅ ከተቋቋሙ የመንሳውያን ስብስብ ጥምረቶች አንድ ወቅት ተቋቁመውና መግለጫ ሰጥተው እንደሚከስም አልያም ስማቸው ብቻ እንደሚቀር ጥምረቶች እንዳይሆን ሥጋት አለኝ ይላል፡፡

ይሁን እንጂ የሞዐ ተዋሕዶ አባሉ ዶክተር ዘርዐየሁ ስሜ ይህን ስጋት አይቀበልም፤ ግብረ ኃይሉ ሲቋቋም ከዚህ በፊት የነበሩ መሰል ማኅበራትንም ሆነ መንፈሳዊ ስብስቦችን ተሞክሮ አይቶ ነው ይላል፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩትን ተሞክሮች መሠረት አድርጎ ግብረኃይሉ የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ እየሠራ መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ዘርዐየሁ፤ ግብረ ኃይሉ ከሌሎች ባለድርሻ ኦርቶዶክሳውያን ጋር ወደፊት ለመሥራት ያቀደውን እንደሚከተለው ያብራራሉ፤ ‹‹ሞዐ ተዋሕዶን አስፈላጊነቱን በተረዳንበት ልክ በተለይ ኦርቶዶክሳዊ እንደመሆኑ መጠን ዋናው ትኩረቱ ቤተ ክርስቲያንን ከህልውና አደጋ ለመታደግ ግብረ ኃይሉ ስትራቴጂ በዝርዝር እንዳስቀመጠ ያመለክታሉ፤ ከዚያም ባለፈ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመዋቅር በአደረጃጀት ደረጃ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት አለ። ከዚህ ውስጥ ደግሞ በርካታ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች አሉ እንዲሁም በሰንበት ትምህርት ቤት እና በብዙ ዓይነት አደረጃጀት የተቋቋሙ ማኅበራት አሉ ከዚህ አንፃር ሞዐ ተዋሕዶ ከነዚህ ሁሉ ባለድርሻ አከላት ጋር ጥምረት ፈጥሮእና አጋዥ ሆኖ ነው የሚመጣው ይላሉ ዶክተር ዘርዐየሁ።

ምክንያቱንም ሲያስረዱ ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ የሚተካው ወይም ሊተካው የሚችል ኃይል የለም ነገር ግን የሚያግዘው የሚደግፈው በተለይ ደግሞ የአጀንዳ አንድነት ኖሮ ማዕከላዊነቱን ጠብቆና ወጥ በሆነ መልኩ ጥያቄዎችን በመፍጠር ችግሮች እንዲፈቱ ግፊት በማድረግ መሥራት ነው›› ይላሉ። የግብረ ኃይሉን ዓላማም ሲያስረዱ ‹‹የመተጋገዝን መንፈስ የመረዳዳትን መንፈስ ለማምጣት ነው በማለትም ይገልጻሉ። ተነጣጥለን ስንቆምና በኅብረት ስንቆም ውጤቱ ይለያል›› የሚሉት ዶክተሩ ‹‹ስለዚህም ኦርቶዶክሳውያን በጋራ የሚቆሙበትን ምዕራፍ መጀመር እንድንችል ነው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝና በመተባበር መንፈስ መሥራት ያስፈለገን ምክንያት›› ሲሉም ይገልጻሉ። ዋናው ቁልፍ ጉዳይ እንደ ግብ የሚነሳውም ዓላማዎቻችንን ለማስፈጸም የምንነሳበትም ‹‹ዋናው ቁልፍ ጉዳይ ይህን ግብረ ኃይል፤ ይህን ኅብረት፤ ይህን የኦርቶዶክሳዊ ስብስብ በሙሉ የጋራ ጉዳይ ኖሮት በአንድ ዓላማ በጋራ መቆም ማስቻል መሆኑንም ይገልጻሉ። በዚህም ሂደት ውስጥ ሞዐ ተዋሕዶ ከሁሉም አካላት ጋራ በመተባበር፣ በመከባበር አብሮ የመሥራት ባሕልን ይዞ የመጣ ነው ሲሉም ያስረዳሉ ዶክተር ዘርዐየሁ።

ግብረ ኃይሉ ዓለማውን ለማሳካት የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ እንደሚንቀሳቀስ የሚናገሩት ዶክተር ወንድወሰን አሰፋ ናቸው። ‹‹የመጀመሪያው ዓላማችን እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ከዘር ፍጅት ማዳን ሲሆን፤ ሁለተኛው በማኅር የተደራጀም ሆነ በግል በየ አጥቢያው የሚንቀሳቀስ ምእመን ለቤተ ክርስቲያን አቅም እንዲሆን እና እኛ ኦርቶዶክሳውያን የሀገር ባለቤትነታችንን ማረጋገጥ ቁልፉ ጉዳዮቻችን ናቸው›› ይላሉ። ግብረ ኃይሉ እነዚህን ወሳኝ ጉዳዮች ለማስፈጸም ሰላማዊና ሕጋዊ መንገዶችን እንደሚከተልም ዶክተር ወንደሰን ያስረዳሉ። ይህንን መንገድ እስከመጨረሻው በትዕግስት ለመከተልም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን የሚሉት የኮሚቴው አባል ዶክተር ወንድወሰን አሰፋ፤ ይሄ በዚህ ሰላማዊ ትግል ጥያቄዎቻችን መልስ ካላገኙ ወደ ሰላማዊ የእንቢተኝነት ትግል እንሄዳለንም ሲሉ ያስረዳሉ፤ የግብ ረኃይሉን የትግል ስልት ባሉን የማኅበራዊ ትስስር ገጾች በየጊዜው ለምእመናን እንናሳውቀለን የሚሉት ዶክተር ወንደሰን የቤተ ክርስቲያን ጥያቄያችን እስኪመለሱ የምንከተለውም ሰላማዊ የትግል ስልት በዓለም ላይ ባልተለመደ መልኩ ኦርቶዶክሳዊ ባህልና ትውፊትን መሠረት ያደረገ እና ኦርቶዶክሳዊ መልክና ይዘት ያለው የአባቶቻችንን ባህልና አስተሳሰብ በሚገልጥ መልኩ እንደሚሆንም ያስረዳሉ።

ኦርቶዶክሳዊያንን ላይ የሚደርሰው ጥቃት ስልታዊ ነው የሚሉት ደግሞ የግብረ ኃይሉ ሌላው የኮሚቴ አባል መምህር ፋንታሁን ዋቄ ናቸው። ስልቱንም ሲገልጡ ‘’ የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ማዳከምና ማፈራረስ፣ ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን የአንድነት አስተምህሮ በምንደኛም በፖለቲከኛም ማላላት፣ የአባቶችን ክብር መቀነስ፣ ኦርቶዶክሳዊ ገበሬዎችን የከተማ ነዋሪዎችን የመግደል የማደህየትና የማፈናቀል ነው’’ ይላሉ። ጥቃቱ ሕጋዊና መዋቅራዊ ሆኖ የሚፈጸም በመሆኑ ትግሉ የሚቀጥለው እነዚህ ስልታዊ ጥቃቶች በሚመጥን አካሄድ በመሄድና ጥቃቱ በዘላቂነት መቆማቸው እስኪረጋገጥ ድረስ ኦርቶዶክሳውያንን አስተባብሮ በመታገል ነው ይላሉ መምህር ፋንታሁን። ትግላችን ፍሬ እስኪያፈራ ብሶታችንን ከሚደግፉ አካላት ሁሉ ጋር እንሰራለን የሚሉት ደግሞ ዶክተር ዘርዐየሁ ስሜ ናቸው።

ዶክተር ዘርዐየሁ እኛ መብታችንን ለማስከበር

ሲንቀሳቀስ የሌሎችን ቤተ እምነቶች መብት ሳንነኩ በመሆኑ አሁን አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ስትነኩ ጥቃት ሲደርስባት በድፍረት ተቆርቁረው የሚናገሩ የሌሎች ቤተ እምነቶች ሰዎችን እያየን ነው ይላሉ፤ ይህም መቆርቆር አንድ በሚያደርጉን የሀገር ግንባታ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ላይ ትግላችንን አንድ አድርገን ለመቀጠል ያስችላሉ ይላሉ::

ሞዐ ተዋሕዶ ዘመኑን በዋጀ ዕውቀት ጠንካራ እንቅስቃሴ በማድረግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ጥያቄዎች ለማስመለስ ከመንግሥት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር መፍትሔ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ሰባት ጥያቄዎችንም ማዘጋጀቱን የኮሚቴው አባላት ይናገራሉ::

### ፯ቱ የኦርቶዶክሳውያን መሠረታዊ ጥያቄዎች

፩ኛ. ‹‹በህገ መንግስት፣ በፖለቲካ ማንፌስቶ፣ በመደበኛ ትምህርት፣ በሚዲያና መሰል መንገዶች ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮንና ኦርቶዶክሳውያንን ለጥቃት የሚያጋልጡ መልእክቶች በአስቸኳይ በሕግ እንዲታገዱ::

፪ኛ. ኦርቶዶክሳውያንን ለይቶ ከሥራ፣ ከመንግስት ኃላፊነት፣ ከሀብት ማፍራት ዕድሎች የሚያገል ከቀበሌ እስከ ፌደራል የተዘረጋው ሃይማኖታዊ መንግስትና መዋቅር በአስቸኳይ እንዲቆምና ሃይማኖታዊ ሳይሆን ሕዝባዊ መሆኑን በተግባር እንዲያረጋግጥ::

፫ኛ. ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በቋንቋና በተለያዩ ዘውጎች ለመከፋፈል የሚደረገው ፖለቲካዊ ጥረት፣በጥናትና ምርምር ስም የሚደረጉ የመከፋፈል ዘመቻዎች እና ተግባራት እንዲታገዱ::

፬ኛ. በኦርቶዶክሳውያን ላይ ያነጣጠረ የአካል፣ የሥነ-ልቦና፣ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ ፣የፖለቲካ ፣የማፈናቀል፣ ከአገራዊ ተሳትፎ የማግለል እና የፍጂት ጥቃቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ::

፭ኛ. እስከ አሁን የተፈጸመው ጥቃት በዝርዝር ተገላጾ አጥፊዎች ለሕግ እንዲቀርቡ እና የተጎዱት እንዲካሱ::

፮ኛ. በመላው አገሪቱ የተፈናቀሉ ኦርቶዶክሳውያን ወደ ቀደመ ቦታቸው እንዲመለሱ ::

፯ኛ."አዲሲቷ ኢትዮጵያ" በሚል ሽፋን ኦርቶዶክሳዊ አሻራዎችን የማጥፋት ፖለቲካዊ ሂደት በአስቸኳይ እንዲገታ እና በግልጽ ይቅርታ ተጠይቆ እርምት እንዲወሰድ:: የሚሉ ናቸው::

ትግሉ ፍሬ እንዲያፈራ ግብረ ኃይሉ መላው ኦርቶዶክሳዊ ከሞዐ ተዋሕዶ ጎን እንዲቆምም ጥሪ አቅርቧል::

ስለ ጥያቄዎቹ የግብረ ኃይሉ የኮሚቴ አባል መምህር ፋንታሁን ዋቄ ሲያብራሩ እንደተናገሩት፤ ‹‹ጥያቄዎቹ የግብረ ኃይሉ የግል ጥያቄዎች አይደሉም:: ብዙ ጥያቄው የሚሊዮኖች ናቸው እንዚህንም መምግሥት በአግባቡ ሊመልስ ይገባዋል:: በመሆኑም ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ጥያቄዎቹ እንዲመለሱ በስብስብ ያሉ ማለትም በማኅበር ደረጃ በሰንበት ትምህርት ቤት፣ በግብርና በትምህርት፣ በመምህርነትና በነጋዴነት ያሉት ሁሉ የራሳቸውን ድርሻ ራሳቸው አስበው ጥያቄዎቹ የሚመለሱበትን ሥራ ለመሥራት መነሳታቸው እንዳለ ሆኖ ግብረ ኃይሉ የሚከተላቸውን የሰላማዊ እንቅስቃሴ ስልት በመከታተል ትግላችንን ለማደናቀፍ የሚሠሩ አካላትን ባለመስማት እና የአጀንዳ አንድነትን በማጽናት ጥያቄዎቹ እንዲመለሱ መሥራት ይጠበቅባቸዋል›› ሲሉም ያሳስባሉ::

# ከስደት መልስ በአርምሞ ያረፈች ነፍስ

**ክፍል ሁለት**

*በካሳሁን ለምለሙ*

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

በወቅቱ እንዲህ ያለ የተሟላ መንፈሳዊ አስተዳደር ያለው ሀገረ ስብከት ስላልነበረ የእርሳቸው ሥራ በአርአያነት ይነሣ ነበር። ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያናችን ካፈራቻቸው ዕውቅ ሊቃውንት መካከል አንዱ በመሆናቸው በየቦታው ያለ ደጋፊ የነበሩ የአብነት መምህራንን ያስታወሱና የደጎሙ የአብነት ትምህርት ቤቶች መስፋፋት እንዲኖር ጥረት ያደረጉ አባት ነበሩ። በመሆኑም የአብነት ትምህርት ቤቶችና የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም የአራቱ ጉባኤ መምህርና ተማሪዎች እና የጎንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ተማሪዎች በቂ ቀለብ እንዲያገኙ አድርገዋል። በሀገረ ስብከታቸው በሚገኙ በዜማና በመጻሕፍት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የቀለብ ችግር ሲገጥማቸው፤ በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁለትና ከዚያ በላይ ተማሪዎች በመደበኛነት እያገለገሉ ቀለብ እንዲያገኙ በማድረግ ለዘመናት ጎልቶ የነበረውን ችግር አቃለዋል።

### ፫. ዘመነ ፕትርክና እና የዓለም አቀፍ ሐዋርያዊ ተልዕኮ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ያህል በፓትርያርክነት ሲመሩ የቆዩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም በዐረፍተ ዘመን መገታታቸውን ተከትሎ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራተኛውን ርእሰ መንበር ለመሠየም ባደረገው ምርጫ በዕጩነት ከቀረቡት ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ የተዘጋጁትን መመዘኛዎች በማሟላትና ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራተኛው ፓትርያርክ ሆነው ተሹመዋል።

በወቅቱ በመራጭነት የተሳተፉት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ የአጠቃላይ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከየሀገረ ስብከቱ የተወጣጡ የሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ተወካዮችና የገዳማትና አድባራት ተወካዮች ሲሆኑ፤ ከእነዚህ አካላት ከፍተኛ የሆነ ድምፅ አግኝተው በመመረጥ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ፬ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ተሹመዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በሀገር ቤት በመንበራቸው የቆዩት ለሦስት ዓመታት ያህል ብቻ ሲሆን የቀሩትን ዓመታት በስደትና ከስደት ተመልሰው በሀገር ቤት ነው። በእነዚህ ጊዜያት የተለያዩ ሐዋርያዊ አገልግሎቶችን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ፈጽመዋል።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

### ፫.፩ የቅዱስነታቸው የሀገር ውስጥ አገልግሎት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ሁነው የተሾሙበት ወቅት ሀገራችን ታላቅ ፈተና ላይ የነበረችበት ነው። በአንድ በኩል ሀገሪቱን የሚመራው መንግሥት የሚከተለው ርእዮተ ዓለም "እግዚአብሔር የለሽ" መሆኑ ቤተ ክርስቲያን ራሷን በራሷ እንድታግዝ ግድ ብሎአት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ገዳማትና አድባራት የጦርነት ቀጠና ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት ምእመናንና ካህናት በችግር አደጋ ላይ በወደቁበት ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን በገቢ ራሷን የምትችልበትን መንገድ አመቻችተዋል። ካህናቱም ከመንፈሳዊው አገልግሎት ጎን ለጎን የተለያዩ ሙያዎችን እንዲቀስሙ አበረታትተዋል፤ ባለፉት ቅዱሳን አባቶች የተጀመረውን የሰበካ ጉባኤ ማደራጀትና የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ማስፋፊያ በሰፊው እንዲከናወን አድርገዋል። ቅዱስ ፓትርያርኩ በዚህ ሳይወሰኑም በወቅቱ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ይካሄድ የነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት ቆሞ ሰላም እንዲሰፍን ጥረት አድርገዋል። ይኸውም

በሀገር ውስጥ ያሉትን የሃይማኖት መሪዎችን በማስተባበር የሰላም ጥሪ ለሁሉ አካላት አቅርበው ነበር።

በወቅቱ በሥልጣን ላይ ለነበረው መንግሥት ቅዱስነታቸው በአካል ተገኝተው የሰላም መልእክት ያቀረቡ ሲሆን፤ በበረሃ ለነበሩት ታጣቂ ኃይሎች ደግሞ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተወካይ እና በሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት በኩል መልእክት እንዲደርስ አድርገዋል። ቅዱስነታቸው ታላላቆቹ የትግራይ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የትግራይ ክፍለ ሀገር ሕዝብ በችግር ላይ በነበሩበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን የበኩሏን ርዳታ እንድታደርግ መመሪያ ሰጥተዋል።

ቅዱስነታቸው የታላቋ ገዳም የርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ካህናት እጅግ ከባድ ችግር ላይ በነበሩበት ወቅት ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድሳት በሚል ስም ለካህናቱ እገዛ እንዲውል አንድ መቶ ሺህ ብር፣ አንድ ተሳቢ የጭነት መኪና እና አንድ ፒክ አፕ መኪና እንዲሰጥ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት በወቅቱ ከነበረው መንግሥት ጋር ለማጋጨት «ገንዘቡን የላኩት ለአክሱም ጽዮን ሳይሆን ለወያኔ ነው» በሚል ከፍተኛ ፈተና ገጥሟቸው ነበር። ቅዱስነታቸው በወቅቱ ሀገራችን ምንም እንኳ በልዩ ልዩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ተወጥራ የነበረች ቢሆንም፤ በተለያዩ አህጉረ ስብከቶች ሐዋርያዊ ጉብኝት በማድረግ የሰላም ግንባታ ማስተማሪያ በማዘጋጀትና ሰባክያነ ወንጌልን በማሰማራት እንዲሁም የገንዘብና የንዋየ ቅድሳት ድጋፍ አድርገዋል። ቅዱስነታቸው በዘመነ ፕትርክናቸው ጊዜ ማለትም ከስደት በፊት የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ አገልግሎት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በመንፈሳዊ ትምህርታቸውና ዕውቀታቸው፣ በምንኩስና ሕይወታቸው የተመሰከረላቸውን ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በአንብሮተ እድ ሾመዋል።

በዚሁ የፕትርክና ዘመናቸው በውጭ ሀገራት በተለይም በምዕራብ ጀርመን ባሉ የተለያዩ ከተሞች እንዲሁም በስዊዘርላንድ ጄኔቫ ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ ትምህርተ ወንጌል ሰጥተዋል። በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በመገኘት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲጠናከር አድርገዋል። በእስራኤል እና በኢትዮጵያ መካከል ተቋርጦ የነበረውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዳግም እንዲቀጥል አድርገዋል። በግሪክ አቴንስ ባደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ በሀገሪቱና በኢትዮጵያ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር አድርገዋል። በውጭ ሀገር ባደረጉዋቸው ሐዋርያዊ ጉዞዎች በየሀገራቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በማጽናናት ቃለ ቡራኬና ቃለ ምዕዳን በመስጠት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲጠናከር አድርገዋል።

### ፫.፪ የቅዱስነታቸው የስደት ዘመን አገልግሎት

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የስደት ታሪክ የሚጀምረው በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ነው። ይኸውም በሀገራችን ኢትዮጵያ በተደረገው የመንግሥት ለውጥ ምክንያት ነው። በወቅቱ በትረ ሥልጣኑን የያዘው ገዢው የኢሕአዴግ መንግሥት ከቅዱስነታቸው ጋር መሥራት እንደማይፈልግና በተለያዩ መንገዶች የሚያደርገው ፖለቲካዊ ጫና እየተባባሰ በመምጣቱና ቅዱስነታቸው በሕይወት እያሉ አዲስ ፓትርያርክ በመሾሙ ወደ ኬንያ ተሰደዋል።

አስከፊው የስደት ሕይወት የሚጠይቀውን ሁሉ እየተጋፈጡ ለአምስት ዓመታት ብዙ ጸዋትወ መከራ ተቀብለዋል። በመቀጠልም ቅዱስነታቸው በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ሰሜን አሜሪካ ዋሺንግተን ሲያትል ግዛት አቀኑ። ከዚያም በካናዳ፣ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በአትላንታ፣ በዴንቨርና በኦሃዮ ግዛቶች ማረፊያቸውን እያደረጉ በመላው ሰሜን አሜሪካ ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን ማከናወን ጀመሩ። ቅዱስነታቸው አብዛኛው ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በጾም በጸሎት እና ምእመናንን ትምህርተ ወንጌል በማስተማር፣ ቃለ ምዕዳን እና ቃለ ቡራኬ በመስጠት ነበር። በተለይም ቅዱስነታቸው ለስብሐተና ማኅሌት በነበራቸው ልዩ ፍቅር ሁል ጊዜ ከሁሉ ቀድመው በመገኘት በፍጹም ትጋትና ተመስጦ ሥርዓተ ማኅሌቱን ይመሩ ነበር።

ቅዱስነታቸው በስደት በነበሩባቸው ዓመታት ሁሉ አብረዋቸው ከተሰደዱ አባቶች ጋር በመወያየት በሰሜን አሜሪካ ከ ፫፻ በላይ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ ጥረት ያደረጉ ሲሆን፣ በተጨማሪም በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአውስትራልያና በኒውዚላንድ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት እንዲመሠረቱ በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰፋ አድርገዋል። በእነዚህ አህጉረ ስብከት ያለውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለማጠናከር ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ዘጠኝ ኤጲስ ቆጶሳትን በዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሾመው ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ደግሞ በካናዳ ቶሮንቶ መንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አራት ኤጲስ ቆጶሳትን በአንብሮተ እድ ሹመዋል። እንዲሁም ሰኔ ፲፪ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም በኦክላንድ ካሊፎርኒያ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ካቴድራል በተጨማሪ ሰባት ኤጲስ ቆጶሳትን በአንብሮተ እድ ሹመዋል። በጊዜው በሀገር ውስጥ ከነበረው ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር የነበረው አለመግባባት የበለጠ እንዳይሰፋ ቅዱስነታቸው አንድም ጊዜ በጉዳዩ ዙሪያ ለጋዜጠኞች መግለጫ ከመስጠት ተቆጥበው የትዕግሥት ባለቤት መሆናቸውን አስመስክረዋል።

### ፬. ከስደት መልስ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሚወዷት ቅድስት ሀገራቸው ኢትዮጵያና ከሚወዱት ሕዝባቸው ተለይተው ለሃያ ስድስት ዓመታት በሐዋርያዊ አገልግሎትና በጸሎት በስደት ከሀገር ውጭ ቆይተዋል። በእነዚህ የስደት ዓመታት ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት፣ ስለ ሀገራቸው ሰላም፣ ፍትሕና ደኅንነት ያለማቋረጥ በመጸለይና ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ዘወትር ተስፋ በማድረግ አምላካቸውን ይማፀኑ ነበር። በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ተቋቁሞ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ሲሠራ የነበረው የሰላምና የአንድነት ጉባኤ ሦስት የሰላምና

የአንድነት ጉባኤያትን ቢያከናውንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ በሁለቱ ሲኖዶሶች መካከል ዕርቀ ሰላም ሳይወርድ ቀርቷል። አራተኛው የሰላምና አንድነት ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በሀገራችን ኢትዮጵያ የመጣውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያን አንድነት ለማጠናከር የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መመለስ ቁልፍ ተግባር መሆኑን አምነው በሁለቱ ሲኖዶሶች መካከል ዕርቀ ሰላም እንዲወርድ ለቅዱስ ሲኖዶስ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ዕርቀ ሰላሙ እንዲከናወን በብፁዓን አባቶች የሚመራ ልዑክ ሰይሟል። በዚህም መነሻነት በሁለቱም ሲኖዶስ መካከል የነበረውን ልዩነት በአራተኛው የሰላምና የአንድነት ጉባኤ አማካይነት ተወግዶ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ታውጇል። ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስቴር) ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት ቅዱስነታቸውንና አብረዋቸው በስደት የነበሩትን ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን ወደ ሀገራቸው ይዘዋቸው ተመልሰዋል። በዚህም ጠቅላይ ሚንስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ያበረከቱት አስተዋጽኦ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁልጊዜ ሲታወስ ይኖራል። ቅዱስነታቸው በመንበረ ፕትርክናቸው ሁነው ከዚህ ዓለም ድካም እስካረፉበት ቀን ድረስ አርምሞ ይዘው ስለ ሀገራቸው፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሕዝብ አንድነት ሲጸልዩ፣ ሲባርኩ ቆይተዋል።

## ፭. ማጠቃለያ

አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሰባት ዓመት በድጓ መምህርነት፣ለበርካታ ዓመታት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በቅኔ ማኅሌትና በቅዳሴ አገልግሎት እንዲሁም በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል፡ ፡ በሊቀ ጵጵስና ከ፲፱፻፸፩ እስከ ፲፱፻፹ ዓ.ም ድረስ በኡጋዴንና በጎንደር አህጉረ ስብከት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገሉ ሲሆን ፓትርያርክነት ደግሞ ከ፲፱፻፹ እስከ ፳፻፲፬ ዓ.ም ቤተ ክርስቲያንንና ሕዝብን ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል፤ የተሰጣቸውን ሐዋርያዊ ኀላፊነትና አደራም በታላቅ ብቃትና በመንፈሳዊ ተጋድሎ ተወጥተዋል። በዚህም በቤተ ክርስቲያናችን የመንበረ ፕትርክና ታሪክ ለ፴፬ ዓመታት ሐዋርያዊና አባታዊ አገልግሎት በመስጠት ረጅሙ አገልግሎት ሁኖ ተመዝግቧል። ቅዱስነታቸው እጅግ በጣም ትጉህ፣ ጠንካራ፣ ለእውነት የቆሙና ላመኑበት ጉዳይ እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ድረስ ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ ነበሩ። ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን በንጽሕናና በቅድስና ያገለገሉ፣ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውንና ቅድስት ሀገራቸውን ኢትዮጵያን የሚወዱ፣ ሥጋዊ ምቾት በሚበዛበት በምዕራቡ ዓለም ሲኖሩ እንኳን ለሥጋዊ ጥቅም ያልተንበረከኩ፣ በምናኔና በልግስና ሕይወት የኖሩ ቅዱስ አባት ነበሩ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከስደት የተመለሱት ስማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ በሚታሰብበት ዕለት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። አሁንም ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ በሚዘከርበት ዕለት የካቲት ፳፭ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈው መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል።

የቅዱስነታቸው በረከት በሁላችን ላይ እንዲያድር እግዚአብሔርን እየጠየቅን ከእኒህ ቅዱስ አባት ታማኝነትን፣ ቅንነትን፣ አገልጋይነትን፣ ሰላምና አንድነት ፈላጊነትን እንማራለን። በዚህ ዓለም ላይ በሕይወተ ሥጋ እስካለን ድረስ እንደ ቅዱስነታቸው ትውልድን የሚቀይር፣ ቤተክርስቲያንን የሚጠቅም ትርጉም ያለው ሥራ ሠርተን ልናልፍ ይገባል። ሕይወታችን ትርጉም የሚኖረው በልካችንና ባለን አቅም ልክ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ትውልድን የሚያንጽ እውነተኛና ትርጉም ያለው ሥራ ስንሠራ ብቻ ነው።

ቅዱስነታቸው ዕድሜ ዘመናቸውን (ከልጅነት እስከ ዕወቀት) ቤተ ክርስቲያናቸውን በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ ተመድበው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። የእርሳቸው የአገልግሎትና የብሕትውና ሕይወት ለዚህ ዘመን ትውልድ ልዩ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት፣ በታማኝነትና በአገልጋይነት ስሜት በማገልገል ሀገርን ሆነ ቤተ ክርስቲያንን ከነክብራቸው ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ የሚያስችለን ነው።

ከቀደሙ አባቶቻችን የምንማረው የሕይወትና የአገልግሎት ትምህርት እውነተኛና ቀጥተኛ ነው እንጂ የተሳሳተ ሀገርን የሚበትን፣ አንድነቷን የሚሸረሽር ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ለአደጋ የሚያጋልጥ አይደለም። አባቶቻችን ሁሌም የቀደመውንና የቀናውን መንገድ ብቻ ስለሚያሳዩን ነው። ቅዱስነታቸውም ለበርካታ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው የበቃውንና የቀደመውን መንገድ እንዲይዙ እንዲሁም ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሱና ሕይወታቸውንም ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጭ እንዳይመሩ አስተምረዋል። በዚህም በልጆቻቸው ላይ መልካም ፍሬን አፍርተዋል።

ከአባቶቻችን እግር ሥር ቁጭ ብለን የምንማረው ትምህርት ራሳችንን በዕውቀት ለመለወጥ ከሚያደርግልን እገዛ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን፣ለሕዝብና አጠቃላይ ለሀገራችን ዕው ቀታችንና ችሎታችን እንዲተርፍ ያደርጋል። እንደቀደሙ አባቶቻችን በውቀትና በሥነ ምግባር ታንጸን ቤተ ክርስቲያንና ሀገራችንን በቅንነትና በታማኝነት ለማገልገል ከልጅነት ዘመናችን ጀምሮ መቅሰም ያለብንን ዕውቀትና ክህሎት ሁሉ በአስተዋይነት ልንቀስም ይገባል። ምክንያቱም ያልተማረ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን ተረክቦ መምራት አይችልምና።

# የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከብ ትውልድ ለማፍራት ጉባኤ ቤቶችን መደገፍ ያስፈልጋል

*በካሣሁን ለምለሙ*

በሀገራችን ኢትዮጵያ ብጥብጥ፣ሁከትና ጦርነት በተከሠተ ቁጥር የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ የምትሆነው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። በተለያዩ ዘመናት ኦርቶዶክስ ጠሎችና አንዳንድ የፖለቲካ ነጋዴዎች የሚያደርሱባት መከራ ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ ያለማቋረጥ ቤተ ክርስቲያንን ለከፋ ጉዳት ምእመናንን ደግሞ ለሞት፣ለአካል ጉዳት፣ለስደት እንዲሁም ለሥነ ልቡና ጫና ሲዳርጉ ቆይተዋል። ዛሬም ውስጣዊና ውጫዊ ጠላቶቿ በሚሰነዝሩባት ጥቃት ዕረፍት አልባ ተቋም አድርገዋታል። በዚህ አራት ዓመታት ውስጥ የተፈጸመባትን ብናስተውል እንኳን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ ቀደም ካሳለፈቻቸው የመከራ ጊዜያት የባሰ እንጂ የተሻለ አይደለም። በሳለፍናቸው ዓመታትና እያሳለፍነው ባለው በእዚህ ዓመት ብቻ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በአክራሪ ሙስሊሞችና በኦርቶዶክስ ጠል ኃይሎች አማካይነት ተቃጥለዋል፤ምእመናን ያለበደላቸው ለሞት፣ለስደት፣ለአከላና ለሥነ ልቡና ጉዳት ተዳርገዋል።

ሰሞኑን እንኳን በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማና አካባቢው አክራሪ እስላሞች በፈጸሙት ጥቃት አራት ነባርና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ ወድመዋል። ዐሥራ ሁለት ምእመናን ሲገደሉ ሰላሳ አንድ ምእመናን ደግሞ ለቀላልና ለከባድ የአካል ጉዳት መዳረጋቸውን የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ ቲቪ) አስታውቋል። አሁንም ድረስ ጉዳት የደረሰባቸው ምእመናንና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቂ የሕክምና አገልግሎት እንዳያገኙ እየተደረጉ መሆኑንም ሀገረ ስብከቱ ማስታወቁ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሠተው ጦርነትም ሌላው በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጠባሳ አስከትሎ ያለፈ ነው። በርካታ መኖሪያ ቤቶች ተጎድተዋል፣አብያተ ክርስቲያናት ወድመዋል፣ የተለያዩ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ንብረታቸው ወድሟል፤ ተዘርፏል፤ ለአካልና ለሥነ ልቡና ጉዳትም ተዳርገዋል። በዚህም ምክንያት ሐዋርያት የሠሯት አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባት በመሆኑ በውስጧ ያሉ መንፈሳዊ ተቋማት ወድመዋል። የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ባስታወቁት መሠረት ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በሀገረ ስብከቱ ከ፸፱ በላይ አብያተ ክርስቲያናት በከፊልና ሙሉ በሙሉ ወድመዋል። ከወደሙ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተቋማት መካከል ደግሞ የአብነት ትምህርት ቤቶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። የአብነት ትምህርት ቤቶች የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከቡ ወጣቶች በዕወቀትና በሥነ ምግባር ታንፀው የሚወጡባቸው መንፈሳዊ ተቋማት ናቸው።

ስለሆነም በዛሬው የቃለ መጠይቅ ዐምዳችን በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በቦሩ ሜዳ ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ቤት የሐዲሳት ትርጓሜ ደቀ መዝሙር የነበሩትንና በዚህ ሰዓት ደግሞ የሳይንት አጅባር ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳደሪ የሆኑትን አባ ዘካርያስ ከፍያለውን እንግዳ አድርገን ጋብዘናቸዋል። እርሳቸውም በጦርነቱ ወቅት በጉባኤ ቤቱ ከጥቂት ደቀመ መዛሙርት ጋር ያሳለፉትን የመከራ ጊዜ በአጭሩ አጫውተውናል። መልካም ንባብ።

**ስምዐ ጽድቅ፡-ሀገረ ስብከቱ በከባድ ጦርነት ውስጥ ባለፈበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ ቢያስታውሱን?**

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** ከጥቅምት ፲፩ እስከ ፲፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ድረስ አካባቢው የጦርነት ቀጠና ሆኖ ቆይቷል። በከባድ መሣሪያ ነውጥ የተረበሸበትና በየቦታው ለምሽግ የሚሆን ጉድጓድ ሲቆፍር የነበረበት ነበር። በዚያ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የግልና የመንግሥት ተቋማት ሙሉ በሙሉ በታጣቂዎች ተዘርፈዋል። የአብነት ተማሪዎችን ጨምሮ የአካባቢው ማኅበረሰብ ለከፋ የምግብ እጥረት ስለተጋለጠ አልፎ አልፎ አካባቢውን ጥሎ በመሰደድ ላይ ነበር። እንዲሁም በጦርነቱ መሀል የተወሰኑ ንጹሓን ዜጎች መጠነኛና የከፋ ጉዳት ደርሶባቸዋል። መቼም የጦርነት ጥሩ ነገር የለውምና የማይሽር ጠባሳ አሳርፎብን ሄዷል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ወቅት የነበረውን ረኀብና ችግር እርስዎና ሌሎች ደቀ መዛሙርት እንዴት አለፋችሁት? ጉባኤ ቤቱ እንዲጠናከር ምን መሠራት አለበት ይላሉ?**

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** በወቅቱ ከማንኛውም ወገን ከየትኛውም አካባቢ ምንም ዓይነት የምግብ አቅርቦት አላገኘንም። ያን ክፉ ጊዜ ያሳለፈነው ከጦርነቱ በፊት ተዘጋጅቶ በተቀመጠ መጠነኛ የጤፍ ዱቄት ነው። ይሁን

እንጂ ከእኔና ከአንድ ዐይነ ሥውር አባት በስተቀር ሌሎች ደቀ መዛሙርት ጦርነቱን በመፍራት ወደ ተለያየ አካባቢ ተሰደዋል፡፡ በወቅቱ ለስምንት ቀናት ያህል ከፍተኛ የሆነ የጭንቅና የመከራ ጊዜ አሳልፈናል፡፡ የነበረንን ምግብ እያብቃቃን በመጠቀም ላይ እያለን ጦርነቱ በመቆሙ ከበጎ አድራጊዎች የተወሰነ ርዳታ ድጋፍ ተደርጎልናል፡፡ በሀገረ ስብከቱ በኩል ደግሞ ደብዳቤ አጽፈንም ረድኤት ድርጅቶች ርዳታ እንዲያደርጉልን በጠየቅነው መሠረት ርዳታ ስለተደረገለን ከዚህ ቀደም ከጉባኤ ቤቱ ወጥተው ተሰደው የነበሩ ደቀ መዛሙርት መመለስ ጀምረዋል፡፡ ሙሉ በሙሉ ውደጉባኤ ቤቱ ያልተመለሱ ደቀ መዛሙርት ቢኖሩም ከረድኤት ድርጅቶች በተደረገልን ርዳታ ስንጠቀም ቆይተን አሁን ላለንበት ሁኔታ ደርሰናል፡፡

ቍጥርም እየጨመረ መምጣቱ በቂና ቋሚ የገቢ ምንጭ ካለተፈጠረ በስተቀር ለወደፊቱ በእኛ ጉባኤ ቤት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ጉባኤ ቤቶች ላይም ከፍተኛ የረኀብ አደጋ ሊከሠት ይችላል፡፡ ሁልጊዜ በልመና በምጽዋት መኖር ሕይወትን ከባድ ስለሚያደርግ ተማሪዎችንና መምህራኑን በበቂ ሁኔታ የሚያስተዳድር በቂ የገቢ ምንጭ መፈጠር አለበት፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ሌሎች ደቀ መዛሙርት ጦርነቱን ፈርተው ሲሰደዱ እርስዎ በጉባኤ ቤቱ ለመቆየት እንዴት ወሰኑ? በዚህ ወቅት ለጉባኤ ቤቱ ድጋፍ እያደረገ ያለው ማን ነው? ደቀ መዛሙርቱ ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲከታተሉ የሚያስፈልጋቸው ምንድን ነው?**



የቦሮ ሥላሴ ጉባኤ ቤት

ከጉባኤ በታቸው ተሰደው እስካሁን ያልተመለሱ ደቀ መዛሙርት እንዲመለሱ ለማድረግና ያሉትም በበቂ ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ጉባኤ ቤቱ ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ (በጀት) ሊኖረው ይገባል፡፡ ጉባኤ ቤቱ እንዳይፈታና ተማሪዎች ያለምንም ችግር ትምህርታቸውን ብቻ እንዲከታተሉ የሚመለከታቸው አካላት የቻሉትን ሁሉ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ዙሪያ የሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና አንዳንድ ግለሰቦች የቻሉትን ሁሉ እያደረጉልን ነበር፡፡ የእነርሱ ድጋፍ ባይኖር ኖሮ ያን ክፉና አስቸጋሪ ጊዜ ማለፍ ባልቻልን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኑሮም እየተወደደ የደቀ መዛሙርቱ

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** እኔ እዚህ እንድቆይ ያደረገኝ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው፡፡ የማመለከው አምላክም አላሳፈረኝምና በእኔም ሆነ በጉባኤ ቤቱ የደረሰ ጉዳት አልነበረም፡፡ በወቅቱ

በርካታ ተማሪዎች ጦርነቱ የሚስከትለውን ችግር ፈርተው በሸሹበት ወቅት እኔም እንድሸሽ ነግረውኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ሽሽት መፍትሔ እንዳልሆነ በመናገር የሚመጣውን መከራ ለመቀበል ወስኘ በጉባኤ ቤቱ ቆይቻለሁ፡፡ ማንንም ተስፋ ሳላደርግ እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ አድርጌ መሥዋዕት ለመሆን ተዘጋጅቼ ነበር፡፡ ነገር ግን ታሪክን የሚቀይረው አምላክ ሳያሳፍረኝ ለዚህች ቀን አብቅቶኛል፡፡ በአካባቢው

ጦርነቱ ከቆመ በኋላም ሰላም ሰፍኖ የተለመደ የዕለት ተዕለት ተግባራችን እየከወን እስካሁን ቆይተናል፡፡ የገቢና የወጪ ያለመመጣጠን ከዚህ ቀደም በጦርነቱ ወቅት ችግር ውስጥ እንድንገባም አድርጎናል፡፡

እስከ አሁኑ ሰዓት ድረስ ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ ከተለያዩ አካላት የዓይነትም ሆነ የገንዘብ ድጎማ ይደረግልናል፡፡ ቢሆንም ግን ይህ በቂና ዘላቂ ነው ብየ አላምንም፡፡ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከብ ትውልድ ለማፍራት ጉባኤ ቤቶችን መደገፍና ተማሪዎችን በዕውቀትና በሥነ ልቡና ማብቃት ተገቢ ነው፡፡ በጉባኤ ቤቱ የሚማሩ ተማሪዎች ከምግብና አልባሳት በተጨማሪ የሕክምና አገልግሎት ወይም የጤና ዋስትና ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህም ሁሉም የበኩሉን ሊያበረክት ይገባል፡፡ ዛሬ ያለተዘራ ዘር ነገ አይታጨድምና ነገ ለምናጭደው ዛሬ ላይ መልካም ዘር መዝራት ያስፈልገናል፡፡ የተዘራው መልካም ዘርም ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን እጅጉን የሚጨነቅና የሚሳሳ ተውልድ ይሆናል፡፡

## ምእመናን ሆኑ አገልጋዮች የዚህን ጉባኤ ቤት ምንነትና አሁን ያለበትን ሁኔታ ተረድተዋል የሚል እምነት የለኝም። ጉባኤ ቤቱ ታሪካዊ፣ጥንታዊና ብዙ ደቀ መዛሙርትን ያፈራ ቢሆነም በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ጭምር ታዋቂ ባለመሆኑ የሚገባውን ያህል ዕውቅናና ድጋፍ እያገኘ አይደለም።

***ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ደቀ መዛሙርት ካሉ ቢገልጹልን? የተሰደዱ ደቀ መዛሙርት ካሉ ወደ ጉባኤ ቤታቸው እንዲመለሱ ምን እየተሠራ ነው?***

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** ተመልሰው ወደ ጉባኤ ቤቱ የመጡ ደቀ መዛሙርት ምንም አይነት የአካልም ሆነ የሥነ ልቡና ጉዳት እንዳልደረሰባቸው በአካል ማረጋገጥ ችለናል፡፡ በስደት ያሉና እስካሁን ያልተመለሱ አንዳንድ ደቀ መዛሙርት የደኅንነት ጉዳይ ደግሞ ስልክ በመደወልና ሰዎችን በመጠያየቅ በተሟላ ደኅንነት ውስጥ እንዳሉ ለመረዳት ችለናል፡፡ በስልክና በመልእክተኛ ደኅንነታቸውን ማረጋገጥ ያልቻልን የተወሰኑ ደቀ መዛሙርት አሉ፡፡ ወንበር ለመዘርጋት፣ለመተካከትና ትምህርት ለመጀመር የተሰደዱ ደቀ መዛሙርት እንዲመለሱ ጥሪ ለማድረግ ቢሞከርም ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአንጻሩ ሌሎች በተለያየ አካባቢዎች እንዲሁ ተሰደው ያሉ ደቀ መዛሙርት ጥሪው ደርሷቸው ለመመለስ ቅድመ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ነግረውናል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ደቀ መዛሙርት የሚሰባሰቡ ከሆነ መደበኛ ትምህርት የምንጀምር ይሆናል፡፡ የሚቀሩ ተማሪዎች የሚኖሩ ከሆነም አፈላልገን ጥሪ እናደርግላቸዋለን፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡- ቀረ የሚሉትና ምእመናን ሊያውቁት ይገባል የሚሉት ሐሳብ ካለ ቢጨምሩልን?***

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** ምእመናን ሆኑ አገልጋዮች የዚህን ጉባኤ ቤት ምንነትና አሁን ያለበትን ሁኔታ ተረድተዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ጉባኤ ቤቱ ታሪካዊ፣ጥንታዊና ብዙ ደቀ መዛሙርትን ያፈራ ቢሆነም በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ጭምር ታዋቂ ባለመሆኑ የሚገባውን ያህል ዕውቅናና ድጋፍ እያገኘ አይደለም፡፡ ብዙ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ቀደም አባቶቻችን በከፈሉት መሥዋዕትነት ጉባኤ ቤቱን አሁን ካለበት ደረጃ አድርሰውታል፡፡ አሁን ያለነው ትውልድ ደግሞ ሚጠበቅብንን በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን የማፍራት ተግባርን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ጉባኤ ቤቶቻችን ላይ ሥራዎች አልተሠራባቸውምና የተሻለ ሥራ ብንሠራ መልካም ነው፡፡ በቀጣይ የጉባኤ ታሪክ በሚገባ ተገልጦ ምእመናንም ሊያውቁት፣ ላላወቀውም ሊያሳውቁት፣ የሚጠበቅባቸውንም ድጋፍም ሊያደርጉለት ይገባል የሚል መልእክት አለኝ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ለነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ይስጥልን፡፡***

**አባ ዘካርያስ ከፍያለው፡-** እኔም ስለ ጋበዛችሁን በእግዚአብሄር ስም አመሰግናለሁ፡፡

# ዳግም ትንሣኤ

ሄለን ገነነ

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን
በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን
አሰሮ ለሰይጣን
አግዐዞ ለአዳም
ሰላም
እም ይእዜሰ
ኮነ
ፍስሓ ወሰላም



የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ትንሣኤ

ልጆች! እንዴት ከረማችሁ? እንኳን ለዳግም ትንሣኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! ልጆች በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ በዓለ ጰራቅሊጦስ ድረስ ሰላምታ የምንለዋወጠው ከላይ በመግቢያው ላይ ባለው መሠረት ነው፡፡ ለዚያም ነው በዚያ ሰላምታ የጀመርነው፡፡ ልጆች እናንተም እስከ በዓለ ጰራቅሊጦስ ድረስ በዚህ መልኩ ሰላምታ መለዋወጥ አለባችሁ እሺ ልጆች!

ልጆች! ባለፈው እትማችን ስለ ሰሙነ ሕማማት ሥርዓትና ትርጓሜ ጽፈንላችሁ ነበረ፡፡ ከዚያ ጽሑፍ ብዙ መንፈሳዊ እውቀት እንዳገኛችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ልጆች ዛሬ ደግሞ ስለዳግማይ ትንሣኤ (ሁለተኛው ትንሣኤ) እና ከትንሣኤ እስከ ዳግም ትንሣኤ ስላሉት ቀናት ስያሜና ትርጉም ቀጥሎ እናቀርብላችኋለን በጽሞና ተከታተሉን፡፡

ልጆች! ዳግም ትንሣኤ ማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ ዓርብ ተሰቅሎ ሞቶ እና ተቀብሮ በዕለተ እሑድ ከመቃብር በተነሣ ጊዜ ለሐዋርያት ተገልጦ ሲታያቸው ቅዱስ ቶማስ በመሀከላቸው አልነበረም፡፡ ሐዋርያትም ቶማስ ከሄደበት በተመለሰ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፤ በመካከላቸውም ተገኝቶ ሰላም እንዳላቸው ሲነግሩት ራሴ በዓይኔ ካላየሁት፤ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ሲሰቀል የተወጋ ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም ብሎአቸው ነበር፡፡

ልጆች! የቶማስን ምላሽ ሰማችሁ! ቶማስ ይህን ያለው ተጠራጣሪ ስለነበረ ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በትንሣኤ ሳምንት ሐዋርያት ተሰብስበው ሳለ በመሀከላቸው ተገልጦ ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎአቸዋል፡፡ በዚያም ሐዋርያው ቶማስ ነበረና ‹‹ ቶማስ ሆይ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን›› አለው፡፡ ቶማስም ‹‹ ጌታዬ አምላኬም›› ብሎ መለሰለት፡፡ ኢየሱስም ‹‹ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚምኑ ብፁዓን ናቸው›› አለው፡፡(ዮሐ. ፳፥፳፰–፳፱)

ልጆች! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስምንተኛው ቀን በዕለተ እሑድ የተገለጠበት ምክንያት ሐዋርያው ቶማስን ለማሳመን ሲሆን፤

ዳግም ትንሣኤ (ሁለተኛው ትንሣኤ) የተባለውም ለሐዋርያት ለሁለተኛ ጊዜ በመገለጡ ነው። ቤተ ክርስቲያንም የትንሣኤ ሳምንት የሆነውን እሑድ ስያሜ ሰጥታ ታከብረዋለች። እኛ ክርስቲያኖችም ዕለተ እሑድን የምናከብራት ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበት እንዲሁም በሳምንቱ ለሐዋርያት የተገለጠባት ክብርት ቀነ ስለሆነች ነው።

ከትንሣኤ እስከ ዳግማይ ትንሣኤ ያሉት ቀናት ስያሜና ትርጉማቸው

ልጆች! ከትንሣኤ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ቀናት የራሳቸው ስያሜና ትርጉም ያላቸው ሲሆን በቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል፡-

**፩. እሑድ ፦** ትንሣኤ ይባላል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ዕለት ስለሆነች በዓለ ትንሣኤ ትባላለች። ልጆች! በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለአይሁድ እንዲያከብሩ ካዘዛቸው በዓላት አንዱ የፋሲካ በዓል ነበር። ይህም ከግብፅ ባርነት የወጡበት ወደ ከነአን የገቡበት (ዘፀ.፲፪፥፩) ነው። በዓሉንም በየዓመቱ የሚያከብሩት ለዚያ መታሰቢያ ነው። በእነዚህ ስምንት ቀናት አይሁድ ሥራ አይሰሩም። በሐዲስ ኪዳን ጌታችን የተሰቀለው በፋሲካ ሳምንት (ማር.፲፬፥፩–፪) ነበረ። በእለተ እሑድ ደግሞ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶአልና(ሉቃ.፳፬፥፩–፯) ዕለቱ ትንሣኤ ትባላለች።

**፪.ሰኞ፦** ማዕዶት ይባላል። ማዕዶት ማለት ‹‹መሻገሪያ›› ማለት ነው። ማዕዶት በዕብራይስጥ «ፓሳሕ» ይባላል። ይህም ማለት ‹‹አልፎ ሔደ›› ማለት ነው። እሥራኤል ዘሥጋ የኤርትራን ባሕር በደረቅ መሻገራቸውን ከግብፅ ወደ ከንዓን መውጣታቸውን፣ ከባርነት መላቀቃቸውን ወደ ነጻነት መሻገራቸውን ያመለክታል። በሐዲስ ኪዳንም ጌታንችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ነፍሳትን ከሲዖል ወደ ገነት ስላሸጋገራቸው ማዕዶት ተብሏል። ነፍሳት ከሰይጣን ቁራኝነት ተላቀዋል። ወደ ነፃነት ተሸጋግረዋል። ፩ኛጴጥ. ፫፥፲፱

**፫.ማክሰኞ፦** ቶማስ ተብሎ ይጠራል። ልጆች ቶማስ ማለት በአረማይክ ቋንቋ ‹‹መንታ›› ማለት ነው። ቶማስ ተጠራጣሪም ነው (ዮሐ. ፳፥፳፬–፳፰) ጌታችን ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ተጠራጥሯልና፡፤

**፬. ረቡዕ፦** አልአዛር ይባላል። አልአዛር የማርታና የማርያም ወንድም የጌታ ወዳጅ ነበረ። ሞቶ በተቀበረ በአራተኛው ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ጠርቶ እንዳስነሣው የሚታሰብበት ነው (ዮሐ.፲፩፥፵፬)። ልጆች! የአልዓዛር ትንሣኤ ለሙታን ትንሣኤ አብነት ነው።

**፭. ሐሙስ፦** የአዳም ሐሙስ ይባላል። አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ በሠሩት ኃጢአት ተጸጽተው ንስሓ ገብተው በመለመናቸው እና እግዚአብሔርም ልመናቸውን፣ ጸሎታቸውን ሰምቶ አዳምን‹‹ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ በሞቴ አድንሃለሁ በማለት ቃል ስለገባለት አዳም ቃል ኪዳን መታሰቢያ ነው።

**፮.ዓርብ፦** ቅድስት ቤተክርስቲያን በመባል ይታወቃል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በመስቀል የጠሰቀለበት እንዲሁም ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የተፈጸሙበት ዕለት ነው።

**፯. ቅዳሜ፦** ቅዱሳት አንስት ተብሎ ይጠራል። ልጆች ቅዳሜ በዕለተ ስቅለት ደረታቸውን እየደቁ፣ እያለቀሱ ይከተሉት የነበሩት (ሉቃ.፳፫.፳፯) እንዲሁም ትንሣኤውን ከሁሉ ቀድመው ያዩት (ሉቃ.፳፥፲) የቅዱሳት አንስት መታሰቢያ ነው።

**፰. እሑድ፦** ዳግማይ ትንሣኤ በመባል ይጠራል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በስምንተኛው ቀን እሑድ ደቀ መዛሙርቱ በር ዘግተው ተቀምጠው ሳለ በተዘጋ ቤት ውስጥ በመግባት ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን››(ዮሐ.፳፥፳፮) በማለት በድጋሚ ስለተገለጸላቸው ዳግማይ ትንሣኤ ተብሏል።

ልጆች! ከዕለተ ትንሣኤ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉትን ቀናትና ስያሜያቸውን በደንብ እንደተረዳችሁ ተስፋ እናደርጋለን። እናንተም የተማራችሁትንና ያወቃችሁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩአቸው እሺ ልጆች! ጎበዞች! በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ። መልካም በዓል ይሁንላችሁ።

# የመከራችን ዋጋ አይርከስ!

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹የሚወደኝ ቢኖር መስቀሌን ተሸክሞ ይከተለኝ›› ብሏል። መስቀል ለእውነት የመቆም፣ እውነትን የማገልገል፣ ስለእውነት መቆም ነው፡፡ እውነት ደግሞ ክርስቶስ፣ ክርስቶሳዊነት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን በተቀበለው መከራና ሞት፣ በኋላ በተገለጠው የትንሣኤ ብርሃን በክርስትና እምነታችን ምክንያት የምንቀበለው መከራ ፍጻሜ አሸናፊነት፣ ክብር፣ ደስታ፣ ጸጋ እንዳለ የሚሰብከን ነው።

ክርስትና በዓለም፣ በመከራ ውስጥ የሚያልፍ ነገር ግን የሚያሸንፍ ሕይወት መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህ የመከራ ሕይወት ሳይለያቸው የኖሩ አኃት አብያተ ክርስቲያናት የዚህ እምነት እና አስተሳሰብ ጣዕሙ አልተለያቸውም። ነገር ግን ነገሥታቱን መሳፍንቱን ጨምሮ አብዛኛው ሕዝብ ክርስቲያን ሆኖ በኖረባቸው ሀገራት/ማኅበረሰቦች ዘንድ ግን ጥቂት መበደል፣ መገፋት እየታየ ስለሰማዕትነት ማሰብ ከሚገባን ክርስቲያናዊ ሐሳብ ሊያወጣን ይታገላል፡፡ ክርስቲያኖች ‹‹በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤›› (ሮሜ ፭፥፱) እንዳለው እንደ መጽሐፉ ቃል በመከራቸው ከፍ ከፍ ይላሉ እንጂ ወደ መከፋት አይሄዱም።

ፖለቲከኞች በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና በምእመናን ላይ በተለየዩ አጋጣሚዎች እያደረሱት ያለው ጥቃት ለክርስቲያኖች በጥንቃቄ መተረጎም ያለበት ነው፡፡ እንደ ዜጋ የምናቀርበው የመብት ጥያቄ ክርስትና ባባህርዩ ከሚጠራው የሰማዕትነት ክብር ጋር እንዳይጋጭ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ የሚደርሱ ስድብና ዘለፋዎች፣ ሤራና ተንኮሎች፣ የምእምናን መገደል፣ የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ የምእመናን እና የካህናት ስደት፣ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችና ይዞታዎች አደጋ ላይ መውደቅ … ወዘተ ለመንፈሳውያን ክርስቲያኖች የዘመነ ሐዋርያትን፣ የሰማዕታትን ዘመን የሕይወት መንፈስ ማስታወሱ በቂ ነው፡፡

ስለክርስቶስ/ስለእምነት/ መከራ መቀበል ለክርስቲያን የደስታም ምንጭ ነው፡፡ ‹‹በመከራችን ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል፡፡›› (፪ኛ ቆሮ ፯፥፬) ስለ ቅዱሳን ሐዋርያት መጽሐፍ ሲናገር ‹‹ሐዋርያትን ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው፥ በኢየሱስ ክርቶስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው፡፡ እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር፡፡›› ይላል (የሐዋ. ፭፥፵፩)፡፡

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በዚህ መንፈስ የሚመራ ነው፣ በዚህ አርኣያነት፣ በዚህ ሕይወት ፈለግ የሚራመድ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን እውነትን ለመመስከር የቆረጠች ናት፡፡ ስለእውነት ታገለግላለች፡፡ ዓለም አገልግሎቷን ይቃወማል፣ ይከሳታል፣ ይዘልፋታል፣ ያሰቃያታል፣ ያሳድዳታል። ይህ ሁሉ ስትቀበልም ለዚያ መከራ የተገባች በመሆኗ ለትውልዱ ጸጋን ክብርን ለማምጣት የተዘጋጀች በመሆኗ በየዘመኑ ያለች ቤተ ክርስቲያን እንደ ሐዋርያ ደስ ይላታል፡፡

ዳግመኛም ሐዋርያው ‹‹አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን›› (ሮሜ ፰፥፲፯) እንዳለው ተስፋ የምናደርገው ክብር መሠረቱ መከራ መቀበል ነው፡፡ ለዚህ ለመከራ የተገቡ መሆን ለሚያምኑ ሁሉ ለበነ መሆኑ የታመነ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ከመከራዋም በኋላ ወደ አገልግሎቷ ትመለሳለች፤ ከመከራ ወደ መከራ ትራመዳለች፤ በዚህ ውስጥ ግን አሸናፊ ማራኪ፤ ኃያል እየሆነች አስፈሪ ሆና ትገለጣለች፡፡

በመሆኑም በየዘመኑ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የሚቀበሉት መከራና የሚያጋጥማቸው ፈተና ሁሉ ክብርን እንደሚያመጣላቸው ያምናሉ፤ ‹‹በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል፤ ያበረታችሁማል፡፡›› (፩ኛጴጥ.፭፥፱) ሐዋርያት በአይሁድ እጅ መከራ እንደተቀበሉ የዚህ ዘመን ክርስቲያኖችም በየሀገሮቻቸው ባሉ ጉልበተኞች መከራ መቀበላቸው አይደንቅም፡፡

የዛሬዎቹ ምእመናን መከራ ከቀደሙት የሚለዩበት ነገር የለም፤ ቀድሞም በጣዖት አምላኪዎች፣ በዓላውያን

ነገሥታት፣ በገንዘብ ወዳዶች፣ በሥልጣን ጥመኞች ይደርሱ ነበር። አሁንም በፖለቲከኞች፣ በኢአማንያን፣ በመናፍቃን፣ በገንዘብ አምላኪዎች ፣ ለሰይጣናዊ ዓላማ በተገዙ ዓለምን በሚወዱ ሰዎች ምክንያት መከራ ይደርስባቸዋል። እነዚህ ወገኖች አሁን በቤተ ክርስቲያንና በቤተሰቦቿ ላይ የሚደርሰውን መከራ የሚያቅዱት/ የሚፈለፍሉት/ የሚመሩት፣ የሚያስፈጽሙት እነሱ ናቸው። ፈተናው በመንደር፣ በሀገር የተወሰነ ብቻ ሳይሆን ዓለምን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር በሚፈልገው ዲያብሎስ የሚፈጸም ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች የመከራው ጠንሳሽ ዲያብሎስ ነው ብለው ካሰቡ በእርሱ ሥራ መንቃት በጸሎት በምጽዋት በስግደት መጠመድ ያስፈልጋል።

የዲያብሎስ ዓላማ ክርስቲያኖች መከራን፣ ችግርን፣ ጉስቁልና፣ ስደት፣ ውርደትን፣ መናቅን፣ መገፋትን ተሰቅቀው ክርስቶስን እንዲተዉ ከዲያብሎሳዊ ሐሳብ ጋር ከዚህ ዓለም ነገር ጋር ብቻ ራሳቸውን እንዲያስተሳስሩ ማስጨነቅ ነው።

ስለዚህ ክርስቲያኖች መከራን በተቀበሉ ጊዜ ሁሉ እንደቀደሙ ሐዋርያት አሸናፊ ስለመሆናቸው፣ ወደ ጸጋና ክብር እየቀረቡ ስለመሆናቸው፣ የቅዱሳን ሐዋርያትና ሰማዕታትን በረከት እየተሳተፉ ስለመሆናቸው ማሰብ እንጂ አንዳንዶች ዛሬ ዛሬ በማኅበራዊ ሚደዲና በሌሎችም ብዙኃን መገናኛ እንደሚያናፍሱት ልቅሶ፣ እንጉርጉሮ፣ የውድቀት ጅማሬ አድርገው በመናገር ከንቱ ስሜት ክርስቲያኖች ውስጥ ማሳደር አስተዛዛቢ ይሆናል።

የመንበረ ፓትርያርክ ክብር ሲደፈር፣ ፓትርያርክ ሲሳደድ ወዘተ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በዚህ መንገድ መከራን ተቀብለው ክብር ያገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እያሰብን ወደ ጸጋና ክብር እየደረስን ነው ልንል ይገባል እንጂ ከንቱ ሥጋዊ ቁጣ፣ ሴራ፣ የሽንፈት መንፈስ ተላብሶ ዐደባባይ ላይ መቆዘም እንዳያስተዛዝበን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ጭራሹኑ በእንግድነት በእጃችን የያዝነው መስቀል የያዘውን መልእክት፣ የያዝንበትንም ዓላማ እና ሕይወት ከትርጉም ያፈነገጠ ያደርገዋል።

ክርስትናን ያለማስመሰል በእውነት ሕይወት አድርግን ለምንይዝ ሁሉ መንገዱ አልጋ በአልጋ አለመሆኑን ለመረዳት ቀላል ይሆናል። መከራ ከክርስቲያን የሚርቀው ከዓለም እና ከኃጢአት ርቀን ለመኖር ስንሞክር ብቻ ነው። ተስማምተን ለመኖር ስንስማማ ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እና ክርስቲያን እውነተኛ ሕይወት መልኩን እየገለጸ ሳለ በሚመጣበት መከራ መነቃቃት እንጂ ለድብርት ለፍዘት፣ ለትካዜ መጋለጥ የለበትም።

ሐዋርያት ፲፪ ሆነው ወጥተው ዓለምን በክርስትና እንዲጥለቀለቅ አድርገውት የነበሩት በመከራ ውስጥ ባገኙት ድል ነው። ለክርስቲያን መከራን መቀበል የአሸናፊነቱ መንገድ ነው። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚወድቀው አገልጋዮች መከራን ሲሳቀቁ፣ መከራ እንዳይደርስባቸው ከዓለም ጋር ሲስማሙ፣ ወይም ዓለምን በመውደድ ክርስትናን ከመከራ የመቀበል ባህሪው ጋር ለማፋታት አመክንዮ ለመደርደር ሲሞክሩ ነው። ይህን ማድረግ ያስተዛዝባል።

በማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን የሚለቀቁ የተለያዩ መልእክቶች ከዚህ አንጻር በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው፡ ፡ አንዳንዶች ባለማወቅ፣ አንዳንዶች ለፖለቲካዊ ጥቅም፣ አንዳንዶች እያወቁም እንዳላወቁ ሆነው ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሱ መከራዎችን እየጠቀሱ ክርስቲያኖችን ተስፋ የሚያስቆርጡ፣ መዓት የወረደባቸው እያስመሰሉ ሙሾ ሲያስወርዱ ይታያል። ቤተ ክርስቲያን እየተቀበለች ያለችውን መከራ መግለጽ ማብራራት አንድ ነገር ሆኖ፣ መከራውን ግን መንፈሳዊ ሕይወትንና ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የተገባች ሆና በመገኘቷ ሊሰማት የሚገባውን መፈሳዊ ሐሴት እየሰወሩ፣ ምእመናን በመጸጸትና በሐዘን በፍርሃት የተሞሉ እንዲሆኑ ጫና ማሳደር አጅግ አስተዛዛቢ ነው።

ከዚህም አልፎ ክርስቲያኖች በሚቀበሉት መከራ ልክ በሌሎች ላይ መከራ እንዲያመጡ የሚያነሣሡ መልእክቶችም በቀጥታ ከክርስትናው መሠረታዊ ዕሳቤ ጋር እንዲላተሙ ያደርጋሉ። ይህ ነገር አሁን እየተለመደ መጥቶ የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች መከራ ጸጋ፣ ኃይል፣ ተስፋና ድል የሚያጎናጽፍ ውድ ነገር መሆኑን እያስረሱ ለመከራው ካሳና ዋጋን ከፖለቲከኞች ሌት ተቀን በመሻት ውዱን ነገር እንዲረክስ በማድረግ ከፍተኛ ትዝብት ላይ የሚጥል ሁኔታ ውስጥ አስገብቶናል። ስለዚህ በጊዜ ታርሞ መከራን የምንተረጉምበት፣ የመንተነትንበት መንገድ እንዱ መጽሐፉ፣ እንደ ሰማእታቱ ገድል፣ እንደሊቃውንቱ ማብራሪያ መሆን ይገባዋል እንላለን።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# በጓደኞቼ ደስተኛ አይደለሁም

***ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? በድኅረ ገጽ የሚቀቀውን የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አነባለሁ። በተለይ ‹‹ምሥጢሬን ዓምድ›› ላይ የሚወጡ ጥያቄዎች እና ለዚያ የሚሰጡ መልሶች በእጅጉ ጠቅመውኛል፤ ብዙም ትምህርት አግኝቼባቸዋለሁ። በእኔም ሕይወት የገጠመኝን ፈተና ላካፍላችሁና ለችግሬ መፍትሔ ትሰጡኛላችሁ በማለት ጥያቄዬን ወደ እናንተ መላክ ፈለግሁ። ይኸውም በሕይወቴ ከባድ ፈተና እየሆነ የመጣብኝ ልባዊ ጓደኝነት መመሥረትና ማጽናት አለመቻሌ ነው። ብዙ ጊዜ የሚያጋጥሙኝ ጓደኞቼ ሲጀምሩና ሲጨርሱ በጠባይ አንድ አይሆኑልኝም። በጊዜ ሂደት የተለያዩ ጠባያትን በማምጣት መልሼ ከጓደኝነት እንዳፈገፍግ ያስገድዱኛል። አብዛኞቹ ምክንያቶቼ ደግሞ መጀመሪያ ላይ ስንቀራረብ የነበሩንን የመንፈሳዊ ሕይወት ጠባያት ከማበርታት ይልቅ ሊሸረሽሩብኝ ሲሞክሩ አገኛቸዋለሁ። አብረን ከጀመርነው እና ከተግባባንበት የመንፈሳዊ ሕይወት እርምጃ ሲያወጡ ያጋጥሙኛል። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ሲጋጥሙ ደግሞ አስመሳዮች እንደሆኑ አስብና ከእነርሱ መራቁን እመርጣለሁ። ይህ ነገር ሲደጋገምብኝ ግን ራሴን መጠየቅ ጀምርኩ። የተሳሳትኩት እኔ ነኝ ወይስ እነሱ ግራ ገባኝ እስቲ እናንተም ሐሳቤን የሚያቃና ምክር ካላችሁ አካፍሉኝ።***

ውድ ጠያቂችን! ያነሡት ጥያቄ ብዙዎች የሚያነሡት፣ ባያነሡትም የሚያብሰለስሉት ጥያቄ እንደሆነ እናምናለን። ጓደኝነት በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ ቁልፍ ሚና አለው። በጓደኞቻችን ምክንያት ልንበረታ ወይም ልንወድቅ እንችላለን። በምንወዳቸው ጓደኞቻችን ምክንያት ከጉዳት ልንድን ወይም ልንጎዳ እንችላለን።

የቅዱሳት መጻሕፍትና የሊቃውንቱ ምክር በዚህ ረገድ ክርስቲያኖች ተጠንቅቀው መራመድ እንዳለባቸው በብርቱ የሚያስረዱ ናቸው። ጠቢቡ በጓደኛ መበታት፣ ክፍ ከፍ ማለት፣ መሻሻል፣ መቃናት እንዳለ ሲያስረዳን ‹‹ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል።›› (ምሳ. ፳፯፥፲፯) እያለ ይመክረናል። በሌላ ወገን ደግሞ አባቱ ዳዊት ‹‹ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።›› (መዝ. ፩ ፥ ፩) ብሎ ያስጠነቅቀናል። የተወደደ የተከበረ ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።››(፩ኛቆሮ.፲፭፥፴፫) እያለ ያስጠነቅቀናል።

ክርስቲያኖች ጓደኝነትን የሚመሠርቱት በእነዚህ ሁለት የሚጠባበቁ አቋሞች መካከል ሆነው ነው። ምርጫቸው ጓደኝነትን ለበጎ ለመልካም ማድረግ ነው። ጓደኞችንም መልካም በጎ ማድረግ ነው። በጓደኝነትም መልካምን በጎውን ነገር ማትረፍ ነው።

ውድ ጠያቂያችን! ይሄንን መሠረታዊ መርኅ ይዘው ጓደኞችዎን በጥንቃቄና ደረጃ በደረጃ መለየት ይጠበቅብዎታል። የቀረበ ሰው ሁሉ እውነተኛ ባልንጀራ /ጓደኛ/ ሊሆን አይችልም። ጓደኝነት ሲመሠረት በመጀመሪያ የትውውቅ /ጊዜያዊ የቀረቤታ ጊዜ/ አለው። በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ ወይም በተለያዩ አጋጣሚዎች አብረውን የሚቆዩ ወይም በዚያ አጋጣሚ ተዋውቀን ለተወሰነ ጊዜ የምናገኛቸው የምናቀርባቸው ጓደኞች ሊኖሩን ይችላሉ። እነዚህ በብዙ አጋጣሚዎች ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ በመሆኑ በቁጥርም ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ የተሻለ ጓደኝነት ግን ከዚህ በተሻለ ሁኔታና ጊዜ ውስጥ ሊመሠረት የሚችል ሲሆን፣ እነዚህ የተዋወቅናቸውን ሰዎች መርጠን በተሻለ ደግሞ የምናቀርብበት ስበት ሊመጣ ይችላል። ከፍላጎቶቻችን፣ ከዓላማዎቻችን፣ ከዝንባሌዎቻችን፣ ከሕይወት መርሆቻችን ጋር በጣም የሚጣጣሙትን ደግሞ ከእነዚያ ከብዙዎች መካከል አንጥረን በተሻለ ቅርበት የምንይዝበት ደረጃም አለ። ‹‹ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤›› የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለዚህም ይጠቅማል። (፩ኛ ተሰ. ፭፥፳-፳፩)።

በዚህ ደረጃ ላይ አብሮ መብላት፣ አንዳንድ ሐሳቦችን ማጋራት፣ በተለዩ የግንኙነት አጋጣሚዎች አብረውን እንዲሆኑ መርጠን አብረናቸው የምንቀመጥ እንሆናለን። በዚህ ደረጃ የለየናቸው ጓደኞች ከቀደመው ደረጃ በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው አይቀርም። ከተዋወቅነው ጋር ሁሉ ምሳ አንበላም፣ አንወያይም፣ አብረን አንቀመጥም። ስለዚህ ከብዙው ጥቂቶቹን ለዚህ እናጫለን። በሂደት እነዚህን ሰዎች በውጣ ውረድ ውስጥ እናያቸዋለን፣ በተለዩ ስሜቶችና አጋጣሚዎች ውስጥ እናጠናቸዋለን። ለአቋሞቻችን፣ ለተግባሮቻችን፣ ለዝንባሌዎቻችን ያላቸው አስተያየትና ግብረ መልስ ምን እንደሚመስል እናጤናለን። ለስሜታችን ቅርብ ለአቋሞቻችን ጥብቅ ድጋፍ፣ ለዓላማዎቻችን ቆራጥ ደጋፊ፣ በችግሮቻችን ደራሽ፣ በሕይወት ስንናወጥ በሚሰጡን ጠቃሚ ምክር አንዳቸውን ከሌላቸው ማበላለጣችን አይቀርም። ይህ ደግሞ ለቀጣዩ የጓደኝነት ደረጃ የምንለያቸውን ምርጥ ጓደኞቻችን ለማግኘት የሚያግዝ ነው።

ውድ ጠያቂያችን እንደ እርስዎ ያሉ ከጓደኝነት አንጻር የልባቸው ሊደርስላቸው ያልቻለና የሕይወት ጥያቄ የሆነባቸው ሰዎች ደግሞ ከዚህ በላይ ሴትም ይሁን ወንድ ባልንጀሮቻቸውን በሚሰጧቸው የጓደኝነት ፍቅር፣ በታማኝነታቸው፣ አብሮ በመኖር ይለያሉ። በጸሎትም ወደ እግዚአብሔር ይማልዳሉ። እንዲህ ሲሆን ‹‹ባልንጀራዬ ማነው? ›› ብለን የምር የምንጠይቅበት ጊዜ ይሆናል ማለት ነው።

በዚህ ሂደት ሦስተኛ ብለን ወደምንጠራው ደረጃ ልንመጣ እንችላለን። ይህ ደረጃ ምናልባትም የልብ ጓደኞቻችንን፣ የቅርብ ጓደኞቻችንን ገንዘብ የምናደርግበት ጊዜ ይሆናል። ዮናታን

ለዳዊት እንደሆነው ያለ መልካም ባልንጀራ የሚገኘው በዚህ ሂደት ነው፡፡ እንደ ዴማስ ያለ አቋመቢስ የሚለየውም በዚህ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተለይተው ባልንጀሮች ያልናቸው ሰዎች ደስታና ኀዘንን የምንነግራቸው /ምሥጢረኞች/ ይሆናሉ፡፡ በሰንበትም በሥራም ጊዜ ልናገኛቸው የምንናፍቃቸው እነሱም ሊያገኙን የሚናፍቁ ጓደኞችህ ናቸው፡፡ ትዕገሥትን፣ ፍቅርን፣ ትሕትናን፣ ጽናትን…ወዘተ መግባቢያቸው ይሆናል፡፡ ለነገሮች በሚሰጡ አስተያየት ላይ የሚቀራረቡ ይሆናል፡፡ ውጣ ውረዶች ከፍ ዝቅ አያደርጓቸውም፡፡ በስሕተትና በበደል ውስጥ ይቅርታን ያውቃሉ፡፡ ከምንም በላይ እግዚአብሔርን በመፍራት አንድ ይሆናሉ፡፡

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎም ሆነ ሌሎች መጠንቀቅ ያለባቸው በዚህ በሦስተኛው ደረጃ ላይ የልብ/ምሥጢረኛ/፣ ሁነኛ ብለን በምንይዘው ጓደኛ ምርጫ ላይ ነው፡፡ እያንዳንዱ የጓደኝነት ደረጃ ሕይወታችን ውስጥ ተጽእኖ የሚኖረው ቢሆንም የልብ ጓደኛ ብለን አምነን የምንከተላቸውና የሚከተሉንን በመምረጥ ደረጃ ላይ ግን ከፍተኛ ማስተዋልና ጸሎት ያሻል፡፡

ምናልባትም ውድ ጠያቂያችን በዚህ ደረጃ ላይ ባደረሷቸው ጓደኞችዎ ምርጫ ላይ የገጠመዎ ፈተና አሁን ላሉበት ደስተኛ ላልሆነ ስሜት የዳረገዎ ይመስለናል፡፡ ስለዚህ ከምንም በላይ በነገ እርምጃዎ ውስጥ እንዚህን ሁኔታዎች ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

ሌላው እርስዎ ዘንድ ሊኖርም ላይኖርም የሚችል ቁልፍ ነገር አለ፡፡ ይህም ለራሳችን ያለን አመለካከት ፈተና እንዳይፈጥርብን ነው፡፡ እኛ ከጓደኞቻችን ብቻ የምንጠብቀው ነገር ኖሮ ለጓደኞቻችን ግን ለመስጠት ካልተዘጋጀን ግንኙነቱ ፈተና ውስጥ ይወድቃል፡፡ ጓደኞችዎ ጠባይ የሚቀየረው በራሳቸው ብቻ ፈቃድና መነሻ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ራስንም መመርመር ይገባል፡ ይህ ሲባል ግን ቀድመው እንዳነሡት ከመንፈሳዊ ሕይወትዎ ላይ ያለዎት አቋም የማይናወጽ ሆኖ ነው፡፡ ምናልባት ግን ከዚህ በመለስ ለጓደኞችዎ የሚጎረብጡ አንዳንድ ድብቅ/ራስዎ እንደበጎ የቆጠሯቸው ጠባያት ካሉ መመርመር፣ ማጥራት ያስፍልጋል፡፡ ‹‹በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ..›› (፪ኛቆሮ ፲፫፥፭) እንደተባለ፤ አስቀድሞም ጠቢቡ ‹‹በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤›› (ምሳ. ፫፥፭) እንዳለ፡፡

ሌላው ጠያቂያችን መጠንቀቅ ያለብዎት የሚመርጧቸው ጓደኞች በራስዎ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ላይ ያላቸው አቋምና አስተያየት ትክክል ባይሆን እንኳን መነሻው ቀናነት ከሆነ በትዕግሥት የሚታለፉ ጉዳዮች የገነቡትን ጓደኝነት የሚንዱ እንዳይሆኑም መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ  ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ለኢዮብ ክፉ ሳይሆኑ ነገር ግን በኢዮብ ላይ የሆነውን ነገር በውል ካለመገንዘብ ያደርሱበት የነበረው ዘለፋና ንዝንዝ ነበር፡፡ ስለእነዚህ ባልንጀሮቹ ግን መጽሐፈ ኢዮብ እንዲህ ሳል ‹‹ሦስቱም የኢዮብ ወዳጆች ይህን የደረሰበትን ክፉ ነገር ሁሉ ሰምተው ከየአገራቸው መጡ፤ እነርሱም ቴማናዊው ኤልፋዝ ፥ ሹሐዊው በልዳዶስ፥ ነዕማታዊው ሶፋር ነበሩ፡፡ እነርሱም ሊያዝኑለትና ሊያጽናኑት በአንድነት ወደ እርሱ ለመምጣት ተስማሙ፡፡ ከሩቅም ሆነው ዓይናቸውን ባነሡ ጊዜ አላወቁትም፤ ድምፃቸውንም አሰምተው አለቀሱ፤ እያንዳንዳቸውም መጐናጸፊያቸውን ቀደዱ ፥ ወደ ላይም ወደ ራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ፡፡ ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ እንደ በዛ አይተዋልና ከእነርሱ አንድ ቃል የሚናገረው አልነበረም፡፡›› (ኢዮ ***፪፥፲፪–፲፫) በኋላ ግን ባለመረዳታቸው ምክንያት የኢ***ዮብን መከራና ትእግሥት እያዩ በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ቃል በመናገራቸው እግዚአብሔር ተቆጣቸው፡፡ እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ነውና የተናገሩበትን፣ የስሕተታቸውን ምክንያት ያውቃልና ማራቸው ኢዮብም እንዲጸልይላቸው አደረገ፡፡ ምህረትም አገኙ፡፡ (ኢዮ 42፥፲)

ውድ ጠያቂችን ጓደኝነት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ፍሬ ነው፡፡ ከሁሉም ጎን ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ የእርስዎ መሠረት የክርስትና ሕይወት መርኖዎች መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡ ይህ ከሆነ ለእርስዎ የሚስማማዎትን ለመምረጥና ለማጽናት ይፋጠኑ፡፡ በዚሁ ልክ የማይገቡና ለሕይወታችን መናድ ምክንያት የሚሆኑትን ደግሞ ፈጥኖ ለማራገፍ አይዘግዩ፡፡

ከማይመስሉዎት ሰዎች በመለየትዎም አይጸጸቱ፤ ብቻዎን እስከሚቀሩም ቢሆን ለመልካም ሕይወትዎ አቋምዎን ያጥብቁ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለልጁ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ማስጠንቀቂያም በልብዎ ይመዝግቡ፤ ‹‹ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ፡፡›› (2ኛ ጢሞ ፫፥ ፪-፭) ብሏልና፡፡

ውድ ጠያቂችን! በሕይወትዎ በሚያጋጥምዎት የጓደኖች ምርጫ ውጣ ውረድ ሁል ጊዜ የምንወስዳቸው ተራ ጥንቃቄዎች ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርም ጥበቃ እንዳለ አስተውሉ፡፡ ይህ ደግሞ የበለጠ በሕይወታችን የሚገለጸው በሚኖረን ጸሎት ሕይወት ውስጥ ነው፡፡ በመሆኑም ስለራስዎም ሆነ ስለባንልንጀሮችዎ ይጸልዩ፡፡ በዚህ ጊዜ ለእርስዎ የሚስማማዎትን ይሰጥዎታል፤ ወይም ያለዎትን ግንኙነት ሁሉ ይባርክልዎታል፡፡ ስለዚህ ለጓደኞች ምርጫ የሚሄዱበትን መንገድ ሁሉ ክርስቲያናዊ በሆነ መልኩ እንዲጠበቅ ይትጉ እንላለን፡፡

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡***